# ደምብ

# MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

**ተዛማጅነት ያላቸው ግብአቶች:** JEA-RB, JED, JED-RE, JEE-RA
**ኃላፊነት ያለበት ጽ/ቤት፡-** Chief of Teaching, Learning, and Schools

## አለም አቀፍ እና የውጭ አገር ተማሪዎች ምዝገባ እና ምደባ

I. **ዓላማ**

የልውውጥ/Exchange እና የውጭ ዓለም አቀፍ ተማሪዎችን በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩል የመቀበል ፖሊሲ "Policy JEA" መሠረት የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት የመኖሪያ፣ የትምህርት ክፍያና ምዝገባ እና "Regulations JEA-RB" የተማሪ ምዝገባ/Enrollment of Students እና "JEA-RE" በትምህርት ክፍያ ላይ የተመሠረተ ምዝገባ/Tuition-based Enrollment.

II. **ትርጉም**

A. አለም አቀፍ ተማሪዎች የሚገለጹት እንደ–

1. ከዩናይትድ ስቴትስ እና ከአዋሳኝ አገሮች ውጭ የሆኑ ተማሪዎች፥ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪነት ያላቸው በዩናይትድ ስቴትስ ወይም በዩ.ኤስ ትምህርት ቤት ሲስተም (ለምሳሌ፡- የመከላከያ ዲፓርትመንት ትምህርት ቤት ወይም እውቅና በተሰጠው በውጭ አገር የሚገኝ አሜሪካን ኢንተርናሽናል ትምህርት ቤት) ውስጥ ባለፉት ሁለት ዓመታት በማናቸውም ጊዜ ትምህርት ያልተከታተሉ።

2. ከሁለት ዓመት በላይ ከዩ.ኤስ ውጪ በሌላ አገር ትምህርት ቤት የተማሩ የዩ.ኤስ ዜጎችን። በዩ.ኤስ የመከላከያ ዲፓርትመንት በሚመሩ፣ ወይም እውቅና በተሰጠው የአሜሪካን ኢንተርናሽናል ትምህርት ቤት "U.S. Department of Defense, or an accredited American International school" የሚሣሰሉ በዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት በሚካሄዱ ትምህርት ቤቶች የተከታተሉትን አይጨምርም።

B. A. የውጭ አገር ተማሪ ማለት፡- ማንኛውም እድሜው(ዋ) ለትምህርት ቤት የደረሰ(ች) እና ለትምህርት ወደ ዩናይትድ ስቴት በቪዛ የመጣ(ች) ተማሪ ማለት ነው።

1. ልውውጥ/Exchange ተማሪ ማለት J-1 ቪዛ (J-1) ያለው/ያላት እና ፈቃድ ባለው ልውውጥ/Exchange ፕሮግራም የታቀፈ(ች) ማለት ነው።

2. ስደተኛ ያልሆነ(ች) ተማሪ ማለት F-1 ቪዛ (F-1) ያለው/ያላት ቢሆንም በ "Immigration and Naturalization Service (INS)" መጽደቅ አለበት።

III. **ቀደምት ሁኔታ/ዳራ**

A. **አለም አቀፍ የምዝገባ እና መግቢያ ጽ/ቤት - The International Admissions and Enrollment Office (IAE)** IAE ስደተኛ ያልሆኑ ጎብኚ የ (F-1) እና የልውውጥ/ **Exchange** (J-1) ተማሪዎችን የመቀበል ህጋዊ

ሂደቶች እና ደምቦች መከበራቸውን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር በ MCPS ብቸኛው ኃላፊነት የተጣለበት ክፍል/ዩኒት ነው።

B. የሚከተሉት ተማሪዎች ወደ MCPS ከመግባታቸው በፊት ወደ IAE መመራት አለባቸው:-

1. አለም አቀፍ ተማሪዎች

2. በ ዩ.ኤስ ትምህርት ቤት፣ እውቅና በተሰጠው አሜሪካን ኢንተርናሽናል ትምህርት ቤት፣ ወይም በ ዩ.ኤስ መንግስት በሚካሄድ ት/ቤት ባለፉት ሁለት ዓመታት በማንኛውም ጊዜ ያልተከታተሉ የዩ.ኤስ ዜጎች።

3. የውጭ አገር ተማሪዎች፣ስደተኛ ያልሆኑ (F-1) እና የልውውጥ/**Exchange** (J-1) ተማሪዎች ጭምር

C. ባለፉት ሁለት ዓመታት በ ዩ.ኤስ ትምህርት ቤት ሲስተም የተከታተለ(ች) ተማሪ ወደ ሆም ስኩል (home school) ወይም ኮንሰርሺያ ጽ/ቤት (consortia office) መግባት ይችላል/ትችላለች።

D. **IAE** የትምህርት ሪኮርዶችን ጨምሮ ሠነዶችን/ዶኩመንቶችን በመተርጎም ድጋፍ ይሰጣል።

E. በ "Metropolitan Association of Foreign Student Advisors (MAFSA) National Grading Scales for grade placement and credit awarding purposes" ድንጋጌ መሠረት ለክፍል ደረጃ ምደባ እና ለክሬዲት አሰጣጥ ዓላማ IAE የውጭ አገር የተማሪዎች ውጤት መግለጫዎችን/ትራንስክሪፕቶችን ይገመግማል።

## IV. ቅደም-ተከተል

A. የወላጅ/የሞግዚት/የስፖንሰር ኃላፊነቶች

1. ማግኘት አለብዎት IAE ተማሪ(ዎች) መገኘት ስለሚኖርባቸው የመቀበያ ቀጠሮ ለመያዝ

2. አዲስ የተማሪ መረጃ ቅጽ ይሙሉ

3. በ "Regulation JEA-RB" ላይ በተደነገገው መሠረት የ IAE ተማሪዎችን ስለመቀበል የመግቢያ ዶኩመንቶችን ያቅርቡ

4. ከዚህ በታች እንደተደነገገው፥ በክፊል እና ወቅታዊ የትምህርት ዓመት እንዲሁም የብሔራዊ ፈተና ውጤቶችን ሪከርድ የያዘ ህጋዊ የመጨረሻ የትምህርት ቤት ሪኮርዶችን ያቅርቡ (አስፈላጊ ከሆነ በህጋዊነት የተተረጎመ ጭምር)

   a) በኤለመንተሪ እና ሚድል ስኩል እድሜ ለሚገኙ ተማሪዎች፥ ተማሪው/ዋ/ዎቹ ባለፈው ዓመት ትምህርት ቤት የተከታተለ(ች)በት ህጋዊ የትምህርት ቤት ሪኮርዶች ያስፈልጋሉ።

   b) የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እድሜ ክልል ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ተማሪው(ዋ) ባለፉት ሦስት ዓመታት ትምህርት ቤት የተከታተለ(ች)በት ህጋዊ ሪኮርዶች ያስፈልጋሉ።

   c) ቅጂዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም፥ ነገር ግን ትምህርት ቤቶች በኢ-ሜይል PDF አባሪ አድርገው ወይም በመደበኛ የፖስታ ቤት አገልግሎት ሪኮርዶቹን በቀጥታ ለ IAE መላክ

ይችላሉ።

d) በመመረቂያ እድሜ ላይ የሚገኙ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ነገር ግን የትምህርት ቤት ሪከርዶቻቸውን ለማቅረብ የማይችሉ ከሆነ፥ ከትምህርት ሚኒስቴር የተጻፈ ደብዳቤ ወይም ተማሪው(ዋ) በመጨረሻ የተከታተለ(ች)በት ትምህርት ቤት ከሚገኝበት ዲስትሪክት ተመጣጣኝ ደረጃ ካለው ባለስልጣን መስሪያ ቤት ተማሪው(ዋ) አለመመረቁ(ቋ)ን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ማቅረብ ያስፈልጋል።

e) በዩ.ኤስ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ጋር የሚመጣጠን እንደ (Cambridge Assessment and International Education program, a transcript review, or national examination) የመሣሰሉ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የውጤት መስጫ/ትራንስክሪፕቶች የመቀበያ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ተጨማሪ ግምገማ ያስፈልጋቸዋል።

B. የ IAE አሠራር/ፕሮሰስ ሃላፊነቶች፦

1. አለም አቀፍ ተማሪዎችን የመቀበል ሒደቶች፦

a) የእያንዳንዱን ተማሪ የተወለደ(ች)በት ቀን እና የክትባት ሪከርድ፣ የወላጅ/ሞግዚት ማንነት፣ መኖርያ፣ እና የተማሪን የቪዛ አቋም መገምገም (አስፈላጊ ከሆነ)

b) ስለ እያንዳንዱ(ዷ) ተማሪ የትምህርት ታሪክ መገምገም፣ የትምህርት ማስረጃዎችን መገምገም፣ የመጨረሻውን/ህጋዊ የትምህርት ቤት ሪከርዶችን መገምገም፣ህጋዊ የትምህርት ቤት ክሬዲቶች እንዲሰጡ ሃሳብ/ሬኮመንዴሽን መስጠት፣ በሜሪላንድ ስቴት እና በ MCPS ደምቦች መሠረት ስለ ትምህርት ቤት ምደባ እና የሚመደብበትን-የምትመደብበትን የክፍል ደረጃ መወሰን።

c) ተማሪው(ዋ) በሌላ የትምህርት ቤት ሲስተም ወደ MCPS ለመግባት የሚያስችልና ከ ዩ.ኤስ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ጋር የሚመጣጠን ትምህርት ማጠናቀቁ(ቋ)ን በመገምገም ይወስናል/ትወስናለች

d) በግላዊ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ የትምህርት ፕሮግራም ወይም ተመጣጣኝ ስነልቦናዊ ወይም የትምህርት ምዘናን ጨምሮ ለስፔሻል ኢጁኬሽን አገልግሎቶች አላማ የእያንዳንዱን ተማሪ ሪከርድ ሠነዶችን/ዶክመንቶችን መገምገም።

እንደዚህ አይነት ዶኮመንት ከተገኘ፥ የ IAE ሱፐርቫይዘር ተማሪው(ዋ) ለመግባት ወደሚችልበት ትምህርት ቤት ርእሰመምህር፣ እንዲሁም ትምህርት ቤቱ ለሚገኝበት የስፔሻል ኢጁኬሽን ክለስተር ሱፐርቫይዘር ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

e) የትምህርት ቤት ቡድኑ ተማሪው(ዋ)ን ወደ ስፔሻል ኢጁኬሽን አገልግሎት መምራት ያስፈልግ እንደሆነ ለማወቅ በመቀበያ ሂደቱ ጊዜ የተገኙ መረጃዎችን መመርመር/መለየት

የ IAE ሱፐርቫይዘር ተማሪው(ዋ) መግባት ለሚችልበት/ለምትችልበት ትምህርት ቤት ርእሰመምህር፥ እንዲሁም በዚያ ትምህርት ቤት ለተመደበ(ች) የስፔሻል ኢጁኬሽን ክለስተር ሱፐርቫይዘር ይህንን መረጃ ሪፖርት ያደርጋል/ታደርጋለች።

f) የ ESOL ተማሪዎች ቀደም ሲል በተለያየ ዘርፍ የወሰዱት የስልጠና ትምህርት ፕሮግራም (Multidisciplinary Education Training and Support (METS) Program) በጣም ውስን ወይም ምንም ያልወሰደ(ች) መሆኑን መለየት።

g) የ IAE መቀበያ እና ማስተላለፊያ ሒደት ማጠናቀቅ

h) ስለ መኖርያ እና የትምህርት ክፍያ/tuition (ተግባራዊ የሚሆን ከሆነ) መወሰድ ያለባቸውን ቀጣይ እርምጃዎች ለወላጅ/ለሞግዚት ማሳወቅ

2. የልውውጥ/Exchange ተማሪዎችን የመቀበል ሒደቶች

a) በተማሪዎች ልውውጥ ፕሮግራም ድርጅት አማካይነት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ህጋዊ ነዋሪነት ካላቸው ቤተሰቦች ጋር ቢበዛ ለሁለት ሰሚስተር ለመቆየት ወደ ዩ.ኤስ ለገቡ የልውውጥ/ኤክስቼንጅ ተማሪዎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በነፃ ትምህርት ይሰጣቸዋል።

b) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከተጠየቀ የታተሙ ሪፖርት ካርዶችን የሚሣሰሉ ይፋ የማይሆኑ ሪኮርዶችን ለኤክስቼንጅ ተማሪ፣ ለእርሱ(ሷ) ወላጆች/ሞግዚቶች፣ ለተቀባይ ቤተሰቦች ወይም ለተማሪ ልውውጥ/ Exchange ድርጅት መስጠት ይቻላል።

c) በአንድ የትምህርት ዓመት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የልውውጥ/ Exchange ተማሪዎች ቁጥር ቢበዛ ከ 50 መብለጥ የለበትም እና በአንድ የ MCPS ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ 5 ተማሪዎች መብለጥ የለበትም።

d) የ IAE ሱፐርቫይዘር የአመልካቹን ብቁነት ከገመገመ(ች) በኋላ አመልካቹ(ቿ) የሚከተሉትን በሙሉ የሚያሟላ/የምታሟላ ከሆነ(ች) ይወስናል/ትወስናለች፣ ያፀድቃል-ታፀድቃለች

(1) የልውውጥ/Exchange ፕሮግራም ድርጅቱ አለም አቀፋዊ የትምህርት ጉዞ መስፈርት የሚያሟላ ስለመሆኑ በካውንስል መፅደቅ አለበት

(2) የልውውጥ/Exchange ፕሮግራም ድርጅቱ በዩናይትድ ስቴትስ የስቴት ዲፓርትመንት "United States Department of State፡ የተሰጡትን የፌደራል ድንጋጌዎች ማክበር አለበት።

(3) የልውውጥ/Exchange ተማሪን ለመመዝገብ እና ለመቀበል የልውውጥ ፕሮግራም ድርጅቱ ተግባራዊ የሚሆኑ የ MCPS ደምቦች እና መመሪያዎችን ማክበር ይኖርበታል።

(4) ኃላፊነት ያለው የልውውጥ/Exchange ፕሮግራም ድርጅት ተወካይ በሞንትጎመሪ ካውንቲ 120 ማይል ጅኦግራፊያዊ ክልል የሚኖር/የምትኖር መሆን አለበት። ይህ ተወካይ በ MCPS ስለተመደበ(ች)ው ተማሪ ኃላፊነት አለበ(ባ)ት።

(5) አመልካቹ(ቿ) ወደ MCPS በሚገባበት-በምትገባበት ወቅት

በሚኖርበት/በምትኖርበት አገር የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራም የሚከታተል/የምትከታተል እና እድሜው(ዋ) ቢያንስ የ15 ዓመት እና ከ 17 ዓመት እድሜ ያልበለጠ(ች) መሆን አለበ(ባ)ት።

(6) አመልካቹ(ቿ) የከፍተኛ ሁለተኛ ትምህርት ቤት ጋር የሚመጣጠን ፕሮግራም ያጠናቀቀ(ች) መሆን የለበ(ባ)ትም። የኤክስቼንጅ ተማሪዎች ለዲፕሎማ፣ ለምረቃ፣ ወይም ለክሬዲት ግምገማ ብቁ አይሆኑም።

(7) የልውውጥ/Exchange ፕሮግራም ድርጅት አመልካቹ(ቿ) ትምህርት ለሚከታተልበት/ለምትከታተልበት ወቅት የሚያገለግል ወቅታዊ J-1 ቪዛ እንዲኖረው/እንዲኖራት እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ህጋዊ/በቋሚነት ነዋሪ ከሆነ ተቀባይ ቤተሰብ ጋር እንደሚኖር/እንደምትኖር ማመቻቸት አለበት።

(a) ማመልከቻው ተቀባይነት ከማግኘቱ በፊት ተቀባይ ቤተሰቦች የተሟላ የወንጀል ማጣራት ሒደት መሙላትና ማጠናቀቅ አለባቸው።

(b) በጊዜያዊነት ከሚቀበሉ ቤተሰቦች ጋር የሚኖሩ አመልካች ተማሪዎችን ማመልከቻ MCPS አያጸድቅም። እጅግ ከባድ/አዳጋች ሁኔታ ተፈጥሮ ተቀባይ ቤተሰብ መቀየር አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ የውጪ የልውውጥ/Exchange ፕሮግራም ድርጅት ተማሪው(ዋ) የጀመረ(ች)በት ትምህርት ቤት ባለበት ክለስተር በዚያው መቀጠል እንዲችል/እንድትችል አዲስ ተቀባይ ቤተሰብ የመፈለግ ኃላፊነት አለበት። ተማሪው(ዋ) ተቀባዩ ቤተሰብ የሚኖሩበትን ማህበረሰብ ወደሚያገለግል ትምህርት ቤት ይላካል/ትላካለች።

(8) የመቀበያው ጊዜ ከአንድ እስከ ሁለት ሴሚስተር ሙሉ ጊዜ ሊሆን ይችላል። ከ MCPS አካደሚያዊ ካለንዳር ተቃራኒውን ከሚጠቀሙ አገሮች የሚመጡ ተማሪዎች በሁለት የተለያዩ አላዳሚያዊ የካላንደር ዓመቶች ሁለት ተከታታይ ሴሚስተሮችን ሊከታተሉ ይችላሉ።

(9) የአመልካቹ(ቿ) ወቅታዊ የቪዛ እና የተወሰዱ ክትባቦች ሁኔታ መረጋገጥ አለበት።

(10) የአመልካቹ(ቿ) የትምህርት ቤት ውጤት B ወይም ከዚያ የተሻለ አማካይ ውጤት ማሳየት አለበት፥ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ።

(11) አመልካቹ(ቿ) መልካም ስነምግባር እንዳለው/እንዳላት እና የተለየ የትምህርት ቤት አካባቢ ጋር የመላመድ ችሎታ እንዳለው/እንዳላት የሚያረጋግጥ የትምህርት ቤት ድጋፍ (ሬኮመንዴሽኖች) ማቅረብ አለበ(ባ)ት።

(12) አመልካቹ(ቿ) የ ESOL ድጋፍ ሳይኖር ትምህርቱ(ቷ)ን በእንግሊዝኛ ለመማር እንደሚችል/እንደምትችል ደረጃ የጠበቀ ምዘና በመውሰድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት እንዳለው/እንዳላት ማሳየት አለበ(ባ)ት።

e) ለቀጣይ የትምህርት ዓመት የልውውጥ/Exchange ተማሪዎችን ማመልከቻዎች እና

ደጋፊ ሠነዶች/ዶኩመንቶችን መቀበል የሚቻለው ከኤፕሪል 15 እስከ ጁን 30 ብቻ ሲሆን፥ እየተካሄደ ባለው የትምህርት ዓመት ለሁለተኛ ሰሚስተር ማመልከቻዎች እና ደጋፊ ሠነዶች/ዶኩመንቶችን መቀበያ ጊዜ ከኦክቶበር 15 እስከ ዲሰምበር 15 ይሆናል። (በ MCPS የልውውጥ/Exchange ተማሪ መቀበያ ማመልከቻ የ MCPS ቅጽ 335-66 ይመልከቱ)

f) የ IAE በ MCPS የልውውጥ/Exchange ተማሪዎች ምዝገባ እና አቀባበል መመሪያ በ MCPS ድረገጽ ላይ ይገኛል።

3. የውጭ ተማሪ አመልካቾች ለ I-20 የማመልከት ሒደት ቅደምተከተሎች Certificate of Eligibility for Nonimmigrant F-1 Student Status (I-20 Form):

a) በትምህርት ዓላማ ብቻ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የመጡ (ወይም ለመምጣት የሚፈልጉ) በሌላ አገር የሚኖሩ የውጭ ተማሪዎች በ MCPS ነዋሪነት የሌላቸው ተብለው ስለሚቆጠሩ እነርሱን ወደ ትምህርት ቤት ለመቀበል የሚቻለው በ. I-20 Form ከተሞላ ብቻ ነው IAE

b) በ MCPS የ I-20 ቅጽ ለማግኘት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡-

(1) የአመልካቹ(ቿ) ወላጆች በዩናይትድ ስቴትስ ነዋሪ አለመሆናቸው።

IAE አመልካቹ(ቿ) ክትባቶችን መውሰዱ(ዷ)ን፣ የቪዛ ሁኔታ፣ እና የአመልካቹ(ቿ) ስፖንሰር በሞንትጎመሪ ካውንቲ ህጋዊ ነዋሪ መሆኑን/መሆናቸውን ያጣራል።

(2) አመልካቹ(ቿ) ቢያንስ 15 ዓመት የሞላው(ት) እና ከ 17 ዓመት እድሜ ያልበለጠ(ች) ቢያንስ ከስምንተኛ ክፍል የሚመጣጠን ትምህርት ያጠናቀቀ(ች) መሆን አለበ(ባ)ት።

(3) በ MCPS Regulation JEE-RA መሠረት፥ ተቀባዩ ትምህርት ቤት የተጨናነቀ አለመሆኑን እና መገኘቱን የተማሪ ዝውውር (Transfer of Students)።

(4) አመልካቹ(ቿ) ያለ ESOL ድጋፍ ትምህርት ለመከታተል የሚችል/የምትችል መሆኑን በታወቀ (የፀደቀ/ተቀባይነት ያለው) የእንግሊዝኛ ቋንቋ ምዘና ብቃት አሳይቷል/አሳይታለች።

(5) የአመልካች የትምህርት ቤት ሪከርዶች B ወይም የተሻለ አማካይ ውጤት፣ ወይም ተመጣጣኝ እንደሆነ ያሣያል።

(6) ስለ ተማሪው(ዋ) መልካም ስነምግባር እና የተለየ የትምርት ቤት አካባቢን የመልመድ ችሎታ እንዳለው-እንዳላት አመልካቹ(ቿ) የትምህርት ቤት ድጋፍ/ሬኮመንዴሽኖች ማቅረብ አለበ(ባ)ት።

(7) በ "I-20 Form" ቅጽ ላይ በተገለጸው መሠረት፥ የአመልካቹ ስፖንሰር ለሚማርበት/ለምትማርበት ያህል ጊዜ የሚሸፍን የትምህርት ክፍያ/tuition በቅድሚያ ይከፍላል/ትከፍላለች።

(8) የአመልካች ስፖንሰር ተማሪው(ዋ)ን በሚያስፈልገው-በሚያስፈልጋት ነገር ለመደገፍ የፋይናንስ አቅም እንዳለው/እንዳላት የሚያረጋግጥ ማስረጃ መስጠት አለበ(ባ)ት።

(9) የአመልካች ስፖንሰር ከአመልካች ወላጆች የተጻፈ የሰነድ ማረጋገጫ ማህተም ያለው ደብዳቤ ማቅረብ አለበ(ባ)ት።

c) የመግቢያ ጊዜ ከአንድ ሙሉ ሴሚስተር እስከ ቢበዛ አንድ የትምህርት ዓመት ሊሆን ይችላል።

d) ለቀጣዩ/መጪው የትምህርት ዓመት የ " I-20 Forms" ማመልከቻዎች ተቀባይነት የሚኖራቸው ከኤፕሪል 15 እስከ ጁን 30 ሲሆን፥ እየተካሄደ ላለው የወቅቱ የትምህርት ዓመት ለሁለተኛ ሰሚስተር ማመልከት የሚቻለው ከኦክቶበር 15 እስከ ዲሰምበር 15 ነው።

e) IAE ስደተኛ ሳይሆኑ የ ዩ.ኤስ የአገር ውስጥ ደህንነት ዲፓርትመንት/U.S. Department of Homeland Security (DHS) ደምቦችን ጠብቀው "I-20 Form" መሙላት የሚጠበቅባቸውን ተማሪዎች የመደገፍ ኃላፊነት አለበት።

C. የአካባቢ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር/ተወካይ ኃላፊነቶች

1. ቀጥተኛ መጠይቆችን፣ እና ጠቅላላ ሠነዶችን/ዶክመንቶችን ማስተላለፍ፣ ከህዝባዊ እና የግል ድርጅቶች እና ሒደቱ ከሚመለከታቸው ግለሰቦች፣ አለም አቀፍ እና የውጭ ተማሪዎች የልውውጥ/Exchange (J-1)" እና ስደተኛ ያልሆኑ (F-1)፣ እና ባለፉት ሁለት ዓመታት በማናቸውም ጊዜ ዩ.ኤስ ትምህርት ቤት ያልተከታተሉ የዩ.ኤስ ዜጎች የሆኑ ተማሪዎችን ለ IAE ምዝገባ፣ እና ምደባ ግምገማ እና ምላሽ መስጠት።

2. በማንኛውም የስደተኝነት ቅጾች ላይ አትፈርም(ሚ)። IAE ማለት በ MCPS በእነዚህ ቅጾች ላይ ለመፈረም ከ DHS ኃላፊነት የተሰጠው ብቸኛ ክፍል/ዩኒት ነው።

3. ሒደቱ በ IAE አማካይነት ከተጠናቀቀ በኋላ ዓለም አቀፋዊ፣ የልውውጥ/Exchange እና ስደተኛ ተማሪዎችን መቀበል። የ IAE ለተወሰነ ጊዜ የት/ቤት መግቢያ ቅጽ/Intake Form ማህተም የተደረገበት ከሆነ፣ "ተማሪው(ዋ) ከመግባቱ(ቷ) በፊት የትምህርት ክፍያ መከፈል አለበት ወይም ክፍያ እንዲቀር በ IAE. መፈቀድ/መፅደቅ አለበት" የትምህርት ክፍያው መከፈሉን ወይም እንዲቀር ከ IAE መፈቀዱን ማረጋገጫ ከ "Division of Controller" ተጨማሪ መግለጫ እስከሚሰጥ ድረስ ተማሪው(ዋ) አይገባም/አትገባም። (ስለ ነዋሪነት እና የትምህርት ክፍያ/Residency and Tuition የ MCPS Regulation JED-RA ይመልከቱ)

4. የተፈቀደላቸውን አካደሚያዊ ፕሮግራም ሲያጠናቅቁ የልውውጥ/Exchange ተማሪዎችን ስተደተኛ ያልሆኑ ተማሪዎችን ማሰናበት።

**ተዛማጅ ምንጮች:** Code of Maryland Regulations §13A.03.02.09

**ስለ ደምቡ ታሪክ፡-** Formerly part of Regulation 560-1 and JED-RA; established as a new, separate regulation August 26, 1987; revised May 2, 1995; revised July 6, 2001; revised September 15, 2003; revised February 24, 2005; revised November 21, 2006; revised April 19, 2011; revised March 5, 2021.